# ወደ ኢትዮጵያ ግዛት የገባው የሱዳን ጦር ጥቃት ሰነዘረ

December 5, 2017

ትላንት ወደ ኢትዮጵያ ግዛት የገባው የሱዳን ጦር ጥቃት መፈጸሙ ታወቀ፡፡ ጥቃቱ በሰዎች ላይ የተፈጸመ ባይሆንም፣ የእህል ክምርን ግን እስከማቃጠል የደረሰ እርምጃ መውሰዱን መረጃዎች ጠቁመዋል፡፡ ጦሩ ትላንት ወደ ኢትዮጵያ ድንበር መግባቱን እና የጦሩን መግባት ተከትሎም የኢትዮጵያ መከላከያ ኃይል ወደ ስፍራው ማምራቱን መዘገባችን ይታወቃል፡፡ የሱዳን ጦር የሉዓላዊ ሀገርን ድንበር አልፎ ቢገባም፣ በህወሓት በሚመራው የኢትዮጵያ መከላከያ ሰራዊት በኩል የተወሰደ እርምጃ የለም፡፡




File Photo

ድርጊቱ በህወሓት መንግስት እና በሱዳን መንግስት ስምምነት የተፈጸመ ካልሆነ በስተቀር፣ አንድ ጦር የአንድን ሀገር ሉዓላዊ ድንበር አልፎ ሲገባ እርምጃ መውሰድ ዓለም ዓቀፍ ህግ ጭምር የሚደግፈው ሀሳብ መሆኑን ታዛቢዎች ይናገራሉ፡፡ ሆኖም የሀገሪቱን የመከላከያ ሰራዊት የአዛዥነት ቦታዎች ተቆጣጥረው የያዙት የህወሓት ጄኔራሎች፣ ድፍረት በፈጸመው የሱዳን ጦር ላይ እስካሁን የወሰዱት እርምጃ የለም፡፡ ከዚያ ይልቅ ከሱዳን መንግስት ጋር ለመነጋገር ወደ ካርቱም ማምራታቸው ነው የተጠቆመው፡፡

ጦሩ በተለይ በምዕራብ ጎንደር አብርሃጅራ የእህል ማሳዎችን በእሳት ማቃጠሉን የሚገልጹት የመረጃ ምንጮች፣ በቀጣይ በሰው ህይወት ላይ ጥቃት ላለመፈጸሙ ምንም ዓይነት ዋስትና እንደሌለም መረጃዎቹ ያክላሉ፡፡ የሱዳን ጦር በኢትዮጵያ ግዛት የሚገኙ ቀበሌዎችን ማለትም ኮረደም፣ ገላዋን እና ኮርመር የተባሉትን ስፍራዎች ተቆጣጥሮ የሚገኝ ሲሆን፣ በአካባቢውም ውጥረት መንገሱ ታውቋል፡፡ የአካባቢው ነዋሪዎች፣ መንግስት ከጥቃት እንዲከላከላቸው ጥሪ እያቀረቡ ቢሆንም፣ በህወሓት ከሚመራው የኢትዮጵያ መንግስት በኩል ግን እስካሁን የረባ እርምጃ አልተወሰደም፡፡